


# የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች

## የእውነተኛ ሰላም ምንጩ እግዚአብሔር ነው

### በቃል የሚጠና፡- የዮሐ. 14፥1

*“ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና፥ ሰላም ለእናንተ ይሁን” (ፊልጵ. 1፥2)።*

### 1 ሰላም ማለት ምን ማለት ነው?

ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ ሰዎች ያቀረበው ሁለተኛው የሰላምታ ቃል፥ *“ሰላም ለእናንተ ይሁን”* የሚለው ነው። አሁንም ይህንን ቃል ጳውሎስ የተጠቀመበት ዝም ብሎ በልማድ ብቻ ሳይሆን፥ ትርጉሙን አውቆ፥ ከልቡ አስቦ የጻፈው የሰላምታ ቃል ነው። ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ አማኞች ያቀረበው ሰላምታ፥ እኔና እናንተ በየመንገዱ ስንገናኝ እጆቻችንን አንስተን *“ሰላም”* እንደምንባባለው ዓይነት የሰላምታ ልውውጥ አይደለም። ሰላምታው ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ አማኞች የእግዚአብሔር ሰላም በሕይወታቸው እንዲበዛላቸው እውነተኛ የሆነውን የልቡን ምኞት ይገልጻል።

*“ሰላም“* የሚለው ቃል በግሪክ ቋንቋ *“ኤይሬኔ”* ሲሆን፥ በዕብራይስጥ ደግሞ “ሻሎም” የሚለው ቃል ነው። *“ሰላም”* ማለት ትክክለኛ ትርጉሙ “ጦርነት” የሌለበት፥ ወይንም ከጦርነት ነጻ የሆነ ማለት አይደለም። *“ሻሎም”* ወይንም *“ሰላም”* ማንኛውም ክርስቲያን በሕይወቱ እንዲኖረው የሚፈልገው፥ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ስጦታ ነው። ክርስቲያኖች፥ እውነተኛ የሆነው “ሰላም” ከሰው ሕይወት ውጪ በሆኑ ሁኔታዎች፥ ወይንም ቁሳቁሳዊ ነገሮች የሚገኝ ነው ብለው አያምኑም። ለምሳሌ፥ አንድ ሰው ጦርነት በሌለበት አገር ውስጥ ሆኖ፥ በኑሮው ተመችቶትና ደልቶት፥ የሚፈልገውን ነገር ሁሉ አግኝቶ የተሟላ ኑሮ ቢኖር እንኳን፥ ያ ሰው “ሰላም” የሌለው መሆን ይችላል። በሌላ በኩል ደግሞ ጦርነት በበዛበት አካባቢ ውስጥ የተጎሳቆለ ኑሮ እየኖረ፥ ሌላው ቀርቶ የዕለት እንጀራውን እንኳን ማግኘት የማይችል ቢሆንም፥ ፍጹም በሆነ ሰላም የተሞላ ሰው መሆን ይችላል። ይህ እንዲህ ሊሆን የሚችልበት ዋናው ምክንያት እውነተኛ ሰላም የሚገኘው በሌላ ነገር ሳይሆን፥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመፈጸም ብቻ ስለሆነ ነው። ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ በመኖር የማይገባንን ነገር ስናደርግ፥ ወይንም መሄድ በማይገባን መንገድ ስንሄድ፥ መምረጥ የማይገባንን ምርጫ ስንመርጥ፥ ህሊናችን እረፍት በማጣት ስለሚጨነቅ፥ ሁል ጊዜ አዕምሯችን ሰላም የሌለው ይሆናል። ነገር ግን በእግዚአብሔር ፈቃድና ምሪት ውስጥ ሆነን የምናደርገው ነገር በጣም አስቸጋሪና ከባድ ቢሆንም፥ በፈቃዳችን ለማድረግ የማንፈልገው ነገር እንኳን ቢሆንም፥ የምናደርገው ነገር እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው ከሆነ፥ በልባችን ውስጥ እውነተኛ እርካታና እንዲሁም ፍጹም የሆነ ሰላም ይሰማናል። እውነተኛው ሰላም እግዚአብሔር ብቻ ሊሰጠን የሚችለው ውስጣዊ ሰላም ነው። በእግዚአብሔር ሰላም ስንሞላ ምንም ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ብንሆንም ልባችንን የተረጋ'ሸ3ና በፍጹም ጸጥታ የተሞላ ይሆናል።

### 2 እውነተኛ ሰላም ከእግዚአብሔር እንጂ ከሰው አይገኝም

ጳውሎስ የፊልጵስዩስ አማኞችን *“ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ሰላም ለእናንተ ይሁን”* ሲላቸው፥ *“ሰላም”* ሰው በራሱ ጉልበትና ችሎታ የሚያገኘው ሳይሆን፥ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ከእግዚአብሔር ጋር ሲታረቅ በውስጡ የሚፈስ የእግዚአብሔር ስጦታ መሆኑን መግለጹ ነው። የእግዚአብሔር ሰላም፥ ከውስጣችን የሚፈልቅ እንጂ፥ በምንይዘውና በምንጨብጠው ቁሳቁሳዊ ነገር፥ ወይንም ከውጪ ባለ ነገር የሚገኝ አይደለም። ኢየሱስ ለእኔና ለእናንተ የሚሰጠን ሰላም ምን ዓይነት እንደሆነ ሲገልጽ *“ሰላምን እተውላችኋለሁ፥ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም። ልባችሁ አይታወክ፤ አይፍራም”* ይላል (የዮሐ. 14፥27)። እዚህ ላይ *“ሰላሜን እሰጣችኋለሁ”* ሲለን፥ ምንም ነገር አይነካችሁም፥ ችግር አያጋጥማችሁም፥ ሁሉ ነገር የተሟላ ይሆንላችኋል፤ የአበባ ምንጣፍ ይነጠፍላችኋል ማለቱ እንዳልሆነ መገንዘብ ያስፈልገናል። በሕይወታችን ከሚያስፈልገን ዋና ዋና ነገሮች መካከል አንደኛው ከውስጣችን የሚፈልቅ ሰላምን ማግኘትን ነው። ሰላም ማጣት ሁልጊዜ ሕይወታችንን በስጋት ይሞላል። ሰላም ማጣት እንቅልፍ አሳጥቶ ያሳድራል፤ የተኛን

ቀስቅሶ ያስነሳል። ሰላም ማጣት፥ የልብ ትርታን እስከሚያቆም ድረስ በፍርሃት ይሞላል። ሰላም ማጣት የሰውን የማሰቢያ አዕምሮ ይቆልፋል፤ ሰውን በትክክል እንዳያስብ ይከለክላል።

ከእግዚአብሔር ጋር ያልታረቀ ሰው ከራሱ ጋርም ያልታረቀ ነው። ስለሆነም በውጪ ካለበት ሁከትና ጦርነት ይልቅ፥ በውስጡ ያለበት ጦርነት ይበልጣል። የሰው ሰላም ማጣት ምክንያት ከውጪ የመጣ ሳይሆን፥ ከውስጡ የመነጨ ነው። የሰላም ማጣት ምክንያት ከውስጣቸው የመነጨ መሆኑን የተረዱት ደግሞ፥ ከራሳቸው ማምለጥ እንደማይችሉ ቢያውቁም፥ ከራሳቸው ለመሸሽ ሙከራ ሲያደርጉ እናያለን። እውነተኛው ሰላም እግዚአብሔር የሚሰጠን ሰላም ነው። ለዚህ ነው ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ አማኞች *"ከእግዚአብሔር ከአባታ ችን ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋናን፥ ሰላም ለእናንተ ይሁን"* ያላቸው። እርሱ የሚሰጠን ሰላም ሁኔታዎች አይወስኑትም፤ ወይንም ከሁኔታዎች ጋር አይለዋወጥም። እግዚአብሔር የሚሰጠን ሰላም፥ ሰውን የከበቡት መጥፎ ሁኔታዎች፥ ወይንም የሚኖርበት የኑሮ ውጥረት፥ ወይንም ችግር አይወስነውም። እውነተኛው ሰላም ዋጋ ከፍለን የምናገኘው ሳይሆን ከክርስቶስ በነጻ የምንቀበለው ስጦታ ነው። ኢየሱስ *"... ሰላምን እተውላችኋለሁ፤ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጣችሁ አይደለም፤ ልባችሁ አታወክ፤ አይፍራም"* ብሎ ያጽናናናል (የዮሐ. 14፥27)። *"ዓለም እንደሚሳጣችሁ"* አይደለም ሲለን፥ ከሁኔታዎች ጋር አይለዋወጥም ማለቱ ነው። ይሄ ሰላም በክብ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጦ በመወያየት የሚገኝ ሰላም አይደለም። የእግዚአብሔር የራሱ ሰላም ነው። በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በልባችን የሚፈስ ነው። ይሄ ሰላም የሰው አዕምሮ ሊያስበው ከሚችለው በላይ ነው። ጳውሎስ ለፊሊጵስዮስ አማኞች የእግዚአብሔርን ሰላም ሲገልጽ፥ *"...አዕምሮን ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል"* ይላል (ፊልጵ. 4፥7)።

## 3 ከዚህ ክፍል የምናገኘው ጠቃሚ ትምህርት

### ሀ ሰላም የሚገኘው የሰላም አለቃ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ልባችን ስናስገባ ነው።

ይሄ ኢየሱስ በእኛና በእግዚአብሔር መካከል በመሆን፥ ከእግዚአብሔር ጋር ሰላም እንድንመሠርት ያደርገናል። *"እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን፥ በእግዚአብሔር ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ"* ይላል (ሮሜ 5፥1)። እውነተኛ ሰላም የሚገኘው ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ግንኙነት ሲኖረን ብቻ ነው።

### ለ በውስጣችን እውነተኛ ሰላም ሊኖር የሚችለው፥ ከህሊና ክስ ንጹህ ስንሆን ነው።

ከህሊና ክስ ነጻ መሆን የምንችለው፥ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ራሳችንን ያስገዛን እንደሆነ፥ እንደ ፈቃዱ መኖር የቻልን እንደሆነ ነው። ኢሳያስ፥ *"በአንተ ላይ ታምናለችና በአንተ ለምትደገፍ ነፍስ ፈጽመህ በሰላም ትጠብቃታለህ"* ይላል (ኢሳ. 26፥3)።

### ሐ "ሰላም አለን" ስንል፥ ምንም ዓይነት መከራ አይደርስብንም ማለት አይደለም።

ኢየሱስ *"በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን፥ አይዟችሁ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ"* ሲለን፥ (የዮሐ. 16፥33) አልፎ አልፎ በመከራ ውስጥ ማለፍ እንደምንችል ሲገልጽልን ነው። ከክርስቶስ ጋር ተጣብቀን ከኖርን በመከራ ውስጥ ብናልፍም እንኳን፥ በእግዚአብሔር መገኘትና በሰጠው ተስፋ ላይ ስለምናርፍ ልባችን በሰላም የተሞላ ይሆናል።

### መ "ሰላም" የእኛ የአማኞች ምርጫ ነው።

መንገዳችን ሻካራ ሲሆንብን፥ ሁኔታዎች የተመቻቹ ሳይሆንልን፥ ደመና ሲከበን፥ ብዙ እንቅፋቶች በመንገዳችን ተዘርግተው ስናይ፥ ለፍርሃትና ለጭንቀት ራሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ የምንፈተንበት ጊዜ አለ። ይሁን እንጂ፥ "እጄን ለፍርሃትና ለጭንቀት አልሰጥም" በማለት በእግዚአብሔር ከታመንን፥ ያኔ ልባችን በሰላም ይሞላል። ይህን ዓይነቱን ፍጹም የሆነውን ሰላም ነው ጳውሎስ የፊልጵስዩስ አማኞች እንዲኖራቸው የተመኘላቸው። በጌታ ፈቃድ ሥር መሆናችንን ስናውቅ፥ በአካባቢያችን ምንም ዓይነት ሁከት ቢኖር፥ በእርሱ ጥበቃ ሥር መሆናችንን አምነን ከተቀበልን፥ ልባችን በሰላም ይሞላል።

---




# የዚህን መጽሐፍ ትንቢት ቃል በማኅተም አትዝጋው።

**(የዮሐ. ራዕይ 22፥10)**




## ሀ የመልእክቱን ፍሬ ሀሳብ ለመረዳት

1. ጳውሎስ የፊልጵስዩስ አማኞችን *“ሰላም ለእናንተ ይሁን”* ሲላቸው ምን መግለጹ ነው?

2. *“ሰላም“* የሚለው ቃል በግሪክ ቋንቋ _____________ ሲሆን፥ በዕብራይስጥ ደግሞ _____________ የሚለው ቃል ነው።

3. እውነተኛ ሰላም የሚገኘው እንዴት ነው?

4. ኢየሱስ ስለ ሰላም የሰጠን ተስፋ ምንድነው? (የዮሐ. 14፥27)

5. ክርስቶስ የሚሰጠን ሰላም ዓለም ከሚሰጠን የሚለየው እንዴት ነው?

6. የሰላም ማጣት ውጤቶች ምንድናቸው?

7. የሰው ሰላም ማጣት ከየት የመጣ ነው?

8. ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ሰላም ለፊልጵስዩስ ሰዎች ሲገልጽ ምን ይላል? (ፊልጵ. 4፥7)

9. ከህሊና ክስ ነጻ መሆን የምንችለው እንዴት ነው?

10. በሰላም መሞላት ከመከራ ሁሉ ነጻ መሆን እንዳልሆነ በምን እናረጋግጣለን? (የዮሐ. 16፥33)

## ለ በዚህ ክፍል ውስጥ ያገኘነውን ትምሕርት በግል ሕይወታችን ለመለማመድ...

1. ከእግዚአብሔር ጋር “ሰላም” እንዳለን በምን እናረጋ ግጣለን?

2. እውነተኛ ሰላም እንዲኖረን ከእግዚአብሔር ጋር ብቻ ሳይሆን፥ ከሰውም ጋር መታረቅ አለብን? በሕይወታችን ያልታረቅነው ሰው አለ?

______________________________
______________________________
______________________________
______________________________
______________________________

3. ካልታረቅነው ሰው ጋር ሰላምን ለመፍጠር ልንወስደው ያሰብነው እርምጃ ምንድነው?


______________________________
______________________________
______________________________
______________________________
______________________________

4. ሰላማችንን የሚሠርቅ፥ ውስጣችንን የሚቆረቁረን ያልተናዘዝነው ኃጢአት ምንድነው?

______________________________
______________________________
______________________________
______________________________
______________________________


5. ለክርስቶስ መጣል ያቃተን ሰላማችንን የሚሰርቅ፥ በውስጣችን ጭንቀትን የሚፈጥርብን ምንድነው?

______________________________
______________________________
______________________________
______________________________
______________________________



**“...የመዳንን ራስ ቁር የመንፈስን ሰይፍ ያዙ፥ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው።...”**

**(ኤፌሶን 6፥17)**



የትምሕርቱ አዘጋጅ
መለሰ ወጉ

# ስንቅና ትጥቅ

**በኢትዮጵያውያን የወንጌል አገልግሎት ተዘጋጅቶ፥ በየሁለት ሳምንቱ እየታተመ የሚወጣ ግላዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ነው።**

**Ethiopian Outreach Ministry**
**P.O.Box 2241**
**York, PA 17405**
**U.S.A.**
**Phone/Fax: (717)846-2041**
**E-Mail: eomusa@aol.com**
**Internet Address:**
**www.ethiopianoutreach.com**

**የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አድራሻ**